እውቁ ድምፃዊ በፈጠራ ክስ እንደተመሰረተበት በወቅቱ ሲዘገብ የቆየ ሲሆን ምስክሮቹን በማስፈራራትና በገንዘብ ደልለው ያመጡዋቸው ቢሆንም የሰጡት ቃል ፍፁም ተመሳሳይነት የሌለውና የሰነድ ማስረጃ የተባለውም የተሰረዘና የተደለዘ መሆኑ እየታወቀ ዳኛው ካድሬ ከወያኔ የተሰጠውን ትዕዛዝ ለመውጣት ሲል ብቻ ጥፋተኛ ብሎ ብይን የሰጠ መሆኑን ተከትሎ ቴዲ አፍሮ የታሰረው በፖለቲካ መሆኑን ያስረዳል ሲሉ የፍርድ ሂደቱን የሚከታተሉ ወገኖች ገልፀዋል::

እውቁ ድምፃዊ በተለይም ምርጫ 1997ን ተከትሎ ባወጣው አዲስ አልበም በወያኔ በድን ጥርስ የተነከሰበት ሲሆን፣ ጊዜውን ጠብቀው የሀሰት ድራማ ሰርተው ለእስር የደረጉት ከመሆኑም በላይ ቁጭታቸውን እየተወጡበት መሆኑን የገለፁት ጉዳዩን የሚከታተሉት ወገኖች መሉ በሙሉ ከሰው መግጨት ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው በፖለቲካ ትዕዛዝ እንዲታሰር መደረጉ ሁሉም ገሀድ ወጥቷል ብለዋል::

ብርቅየ ወጣቱ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሣሁን ጉዳዩ በፍርድ ሂደት ላይ ነው ተብሎ ባለበት ሰዓት በቴሌቭዥንም ሆነ በሬዲዮ የሱ ስራዎች እንዳይለቀቁ የታገዱ መሆኑን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ዘገባ ገለፀ::

የእውቁ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሣሁን ዘፈኖች ከሐምሌ 14 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ በመንግስት መገናኛ ብዙሃን በተባሉት ወያኔ እንደልቡ በሚጨፍርባቸው ሬዲዮና ቴሌቭዥን እንዳይስተናገዱ ወይም እንዳይለቀቁ የታገደ መሆኑን የገለፁት ምንጮች ትዕዛዙ የመጣው ከማስታወቂያ ሚኒስትሩ ከብአዴኑ ብርሀን ኃይሉ መሆኑንም አጋልጠዋል::

ቴዲ የታሰረው በፖለቲካ ምክንያት መሆኑን ያጋለጠው የወያኔ ድርጊት እስከ ዛሬ የሀሰተኛ ድራማ ለመስራት ቢሞክሩም ያልተሳካላቸው መሆኑን ሲያረጋግጡ ይፋ አድርገው ያወጡት መሆኑን የጠቆሙት መንጮቹ የቴዲ ዘፈኖች እንዳይዘፈኑ መታገዱ እራሱ እጅግ አስገራሚና ሕግ አልባ ሀገር ውስጥ መኖራችንን ያረጋገጠ ነው ብለዋል::

ለዋለው ውለታ ጉንፋን እንኩዋን ሲይዘው በሕዝብ ገንዘብ አሜሪካ ታክሞ የሚመጣው የወያኔው ዳኛ ልዑል ገ/ማሪያም እራሱ በሰጠው ትዕዛዝ ብቻ ጋዜጠኛ መስፍን ነጋሽንና ጠበቃ ሚሊዮን አሰፋን እራሱ ከስሶ፣ እራሱ አቃቤ ሕግ ሆኖ እራሱ ዳኛ ሆኖ በተሰየመበት ችሎት አስቀርቧቸው ቅጣት መወሰኑ ሰውየው የበላይ አለቃ የሌለው አዛዡ እሱ መሆኑን የተረዳንበት ወቅት ነው ሲሉ ጉደዩን በቅርበት የሚከታተሉት ወገኖች አስረድተዋል::

የወያኔ ቡድን ገመናየን ለምን አጋለጠብኝ በማለት ለ3 ዓመታት ያህል ሲያደባ ቆይቶ የሀሰተኛ ድራማ ሲያዘጋጅ ከርሞ ባልተጠበቀና ባልታሰበ ወቅት ቴዲ አፍሮን ጠልፎ ለመጣል ያደረገው ሙከራ ለጊዜው የተሳካለት ቢሆንም የህዝብ ድጋፍና ፍቅር ያለው መሆኑን በመረዳታቸው ስራዎቹ በሬዲዮና ቴሌቭዥን እንዳይተላለፉ መወሰኑ ታውቋል::

የቴዲ ዘፈኖች በሬዲዮና በቴሌቭዥን እንዳይተላለፉ ትዕዛዝ የሰጠው የወያኔ ቡድን ምስጥሩን ለሕዝብ ደብቆ የቆየ ቢሆንም አሁን ደግሞ ከመቼውም ጊዜ በላይ ደረቱን ነፍቶ እንደ ሰፈር ውስጥ አውደልዳይ እየተገላበጠ የሀገሪቱን ዜጐች እያሰረና እየፈታ የሚያስቃይ ቡድን ነው ሲሉም ይገልፃሉ::

የቴዲ የፍርድ ሂደት ትክክል አይደለም ክሱ ሲመሰረት ሊያሟላ የሚገባውን አላሟላም ብለው ትችት ሲሰነዝሩ የነበሩትን የሕግ ባለሙያዎች የወያኔ ደህንነቶች በስውርም ሆነ በቀጥታ እያስፈራርዋቸው ትንፍሽ እንዳይሉ ያደረጉ ሲሆን፣አሁን ደግሞ ሀገር ያወቀውን ፀሐይ የሞቀውን እውነት በመካድ ጋዜጠኛ እና የሕግ ባለሙያዎችን ማዋከባቸው ሰዎቹ እያበዱ መሆናቸውን ያስረዳል ሲሉም ይተቻሉ:የቴዲ ስም መነሳት እሬት የሆነባቸው ወያኔዎች በንዴት በጠበቃው እና በጋዜጠኛ ው ላይ የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥተው ውሳኔ አስተላልፈዋል::

ሁለቱም ግለሰቦች አንደኛ ተከሳሽና ሁለተኛ ተከሳሽ በሚል ከፋፍለው 1ኛ የቴዲ ጠበቃ ሚሊዮን አሰፋ 2ኛ ጋዜጠኛ መስፍን ነጋሽ ተብሎ በዓለም ላይ ተሰመቶና ተደርጐ በማይታወቅ ሁኔታ «የፍርድ ሂደቱን በማወክ» በሚል ብቻ ጠበቃውን የ50 ቀናት እስራት ጋዜጠኛውን ደግሞ የ1ወር እስራት በሁለት አመት ገደብ የተቀጣ መሆኑ ታውቋል::

ከሣሽ ልዑል ገ/ማሪያም፣ አቃቤ ሕግ እራሱ፣ ዳኛ እራሱ ልዑል ሆኖ አድራጊ ፈጣራ ያለ እኔ የለም በሚል በሁለቱም ላይ ቅጣት ያስተላለፈ ሲሆን፣ ይህንን የፍርድ ሂደት የተከታተሉ የሕግ ባለሙያዎች ቀድሞ በሀሪቱ ሕግ አልነበረም :: አሁን ደግሞ የባሰ ወደ መቃብር ወርዱዋል ሲሉ ተስፋ በቆረጠ ሁኔታ ሲገልፁ ተደምጠዋል::

በቴዲ ላይ የመሰከረው ኩባዊ ሀሰተኛ ምስክር ቃል ስለሰጠ እከሣለሁ የፍርድ ሂደቱም አድልኦ የተሞላበት ነው ብለው ጠበቃው በመናገራቸውና ይህንኑ ሕዝብ ሐሳቡን በነፃ መግለፅ አለበት የሚለውን ተግባራዊ ያደረገ ጋዜጠኛ ላይ ቅጣት መወሰኑ በእጅጉ አሳዛኝና ሕግ አልባ ጥቂት ግለሰቦች የፈለጉትን ማድረግ የሚችሉበት ሀገር ውስጥ መኖራችንንም ከመቼውም ጊዜ በላይ ተረድተናል ሲሉ እነኚሁ የሕግ ባለሙያዎች በአግራሞት ገልፀዋል::

የቴዲ ጠበቃ 1ወር ከ20 ቀን ስለተፈረደባቸው ወደ ቃሊቲ እስር ቤት የተላኩ ሲሆን ጋዜጠኛ መስፍን የአንድ ወር እስራት በሁለት ዓመት ገደብ ተጥሎበት ተለቅቋል:: ይህ ማለት በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ተመሳሳይ ተግባር ፈፅመሀል ብለው እነ ልዑል ቢጠሩት ያለምንም ክርክር የአንድ ወር እስራቱ ተግባራዊ እንደሚሆን ነው ሲሉም እነኚሁ የሕግ ባለሙያዎች ይገልፃሉ::

ጋዜጠኞች የሕዝብን ሐሳብ ይፋ እንዳያደርጉና የተደበቀ የወያኔን ገመና አጋልጠው እንዳያወጡ አንገታቸውን ደፍተው እንዲኖሩ ለማድረግ የተወሰደ እርምጃ ነው ያሉት አንድ የሕግ ባለሙያ ከዚህ

ወዲያ አንዲትም እንቅስቃሴ ማድረግ ወንጀል በመሆኑ የነፃ ፕሬስ ጋዜጣዎች በሀገሪቱ ቀድሞም አልነበሩ አሁን ያሉትም ሁለትና ሶስት የሆኑትም ስራቸውን እንዲያቆሙ የማስጠንቀቂያ ደወል ነው የተደረገላቸው ሲሉ እኚሁ የህግ ባለሙያ ገልፀዋል:::

የቴዲ አፍሮ የክስ ሂደት ስትከታተል የነበረችው እንቁ መፅሄት ለ2 ወራት ያህል በእስር ቤት ታግታ የተለቀቀች ሲሆን፣ ጋዜጠኞቹም ለ15 ቀናት ያህል በእስር ቤት ታሽተው በዋስ መለቀቃቸው ይታወሳል::

አሁንም በቴዲ አፍሮ ዙሪያ የሚዘግብ ጋዜጠኛ ካለ ወደ እስር ቤት እንደሚጓዝ ለየጋዜጦቹ ዝግጅት ክፍል ትዕዛዝ በስልክ የተሰጠ ሲሆን፣ የመንግስት ሚዲያ ላይ የሚሰሩትም የቴዲ ዘፈኖች እንዳይስተናገዱ ጥብቅ መመሪያና ትዕዛዝ መሰጠቱ ወያኔ በቴዲ ላይ የጀመረውን ፖለቲካዊ ጉዞ እያጠናከረ መሆኑን የሚያመላክት ነው ሲሉም ገልፀዋል::

የወያኔው አረመኔ ቡድን በቅርቡ የመገናኛ ብዙሃንና የፕሬስ ሕግ ብሎ በአለም ላይ የመጀመሪያ አፋኝና ጨቋኝ ሕግ አፅድቆ በማግስቱ ጋዜጠኞችን የማሰርና የማዋከብ ዘመቻ ከመጀመሩም በላይ የሚሰሯቸውን ስራዎች በየማተሚያ ቤቱ ባስቀመጡዋቸው ሰላዮች አማካኝነት ቁጥጥር መጀመራቸው ታውቋል::
በቅርቡ በፀደቀው የሕዝብን አንደበት የሚሸብበው ይኸው የፕሬስ ሕግ በሁሉም መልኩ ነፃነት የሚያሳጣ ከመሆኑም በላይ የማያላውስ መሆኑን የገለፁት አንድ የሕግ ባለሙያ ወያኔ ለእራሴ ብቻ እያለ እራሱን አሳብጦ ሊፈነዳ የተቃረበበት ወቅት ላይ የደረሰ ይመስላል ሲሉም አስተያየታቸውን ሰንዝረዋል::

ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል የሆነበት የወያኔ ቡድን አፍላ ፍቅር ከሻዕቢያ ጋር በገባበት ወቅት የኢትዮጵያን ድንበር እንደገና ዳቦ ቆርሶ ካስረከበ በኋላ መልሶ ፍቅራቸው ሲቀዘቅዝ የጀመሩት ጦርነት አሁንም እያረገሸ ከፍተኛ ችግር ውስጥ ሊዘፈቁ መሆኑን የወታደራዊ ባለሙያዎች ስጋታቸውን እየገለፁ ይገኛሉ::

ባለፈው ሳምንት ውስጥ የተባበሩት መንግስታት ፀጥታ አስከባሪ አንሚ ለ8 ዓመታት ያህል በሁለቱ ሀገሮች ድንበር ላይ ሰፍሮ ቢቆይም ለውጥ ያልመጣ በመሆኑ ስፍራውን ለቅቆ ተልዕኮዬን ጨርሻለሁ ብሎ ይፋ መግለጫ ከሰጠ በሁዋላ በሁለቱም ሀገሮች በኩል የጦርነት ነጋሪት እየተጐሰመ መሆኑን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ::

በዚሁ ባሳለፍነው ሳምንት ውስጥ የወያኔ ቡድን ከፍተኛ የወታደራዊ ቅስቀሳ በቴሌቭዥን እያደረገ ሲሆን፣ በተጓዳኝም በድብቅ በየጦሩ ካምፕ ውስጥ ሲያሰለጥን የነበረውን ጦር አስመርቆ ወደ ግንባር እየላከ መሆኑን ምንጮቹ ገልፀዋል::

ቅዳሜ ሐምሌ 26 ቀን 2000 ዓ.ም በጐጃም ውስጥ በሚገኘው ብርሽለቆ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ ውስጥ ለ4 ወራት ወታደራዊ ትምህርት ሲሰጣቸው የነበሩትን 10 ሺህ ወታደሮች ያስመረቀ ሲሆን፣ሲያሰለጥኗቸው የነበሩት አሰልጣኞችም ወደ አውደ ዉጊያው እንዲሄዱ መደረጉን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋልጠዋል።

በእብሪትና በትዕቢት የተወጠሩት የወያኔ መሪዎች በህዝብ ሕይወትና ንብረት እየቀለዱ ከ100 ሺህ በላይ ዜጐችን አስጨርሰው ዛሬም ከዚያ በከፋና በባሰ መልኩ ለማስጨረስ መጣዳፋቸው ያሳዝናል ያሉት አንድ የወያኔ የጦር መኮንን በአሁን ሰዓት በየጦር ክፍሉ ውስጥ እየተረደገ ያለው ዝግጅት ሀገሪቱ ከምትችለው በላይ ኢኮኖሚዋን የሚያደቅ ነው ሲሉም ገልፀዋል።

ሰሞኑን ቻይና ሰራሽ የሆኑ አዲስ የጦር መሣሪያዎችን በጐጃም በኩልና በአወሽ አርባ ዱብቲ መሰመር ሌሊት እየተጓጓዘ መሆኑን የገለፁት ውስጥ አዋቂ ምነጮች ወያኔ ህዝቡ ተርቦ የሚላስ የሚቀመስ አጥቶ በየቀኑ የሰው ልጅ እንደ ቅጠል እየረገፈ ባለበት በዚህ ቀውጢ ወቅት በውድ ዋጋ በውጭ ምንዛሪ ከቻይና የጦር መሣሪያ እያስገባ መሆኑ ማሰቢያ የሌላቸው ግለሰቦች የተጠራቀሙበት ቡድን መሆኑን ያረጋግጣል ሲሉ ገልፀዋል።

በሀገሪቱ ውስጥ ያሉት የጦሩ ባልደረቦች ሁሉም በያሉበት በተጠንቀቅ እንዲዘጋጁ ከመከላከያ ኢታማዦር ሹም ጄኔራል ሳሞራ የኑስ ትዕዛዝ የተሰጣቸው መሆኑን የጠቆሙት ምንጮች በተለይም በየወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ ውስጥ የነበሩ አሰልጣኞች ሳይቀር ወደ ዉጊያው እንዲሄድ መደረጉንም ምንጮቹ አጋልጠዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከዚህ ቀደም ለሀገራችንና ለድንበራችን ማስከበር እስከ ሕይወት መስዋዕትነት እንከፍላለን ብለው ዘምተው የነበሩ የቀድሞ ጦር አባላት ያለ ጡረታ የተባረሩ ሲሆን፣ ሰሞኑን ደግሞ ጥሪ እንደተደረገላቸው ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ።

ያለ ጡረታና አበል ከባድመ ውጊያ በሁዋላ የተባረሩት የጦሩ አባላት እስከ ዛሬ ዞር ብለው ያላዩቸው ወያኔዎች ችግሩ ሲፀናባቸው የድረሱልኝ ጥሪ ማድረጋቸውን የገለፁት ምንጮች በተደረገው ጥሪ መሠረት አንድም የቀድሞ ጦር አባል እንደልተመዘገበ የውስጥ አዋቂ ምንጮች ዘገባ ያስረዳል።

የወያኔ ሰው በላ ቡድን የሰውን ልጅ እንደ ሸቀጥ አንዴ ወደ ወዲያ አንዴ ወደዚህ እያደረገ እንዳሻው የስልጣን እድሜውን ለማራዘም እየተፍጨረጨረ ቢሆንም ዋሾ መሆኑን የተረዱት የቀድሞ ጦር አባላት የተደረገላቸውን ጥሪ ሳይቀበሉ ውድቅ ማድረጋቸውን ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል።

በሰሜን ከሻዕቢያ ጋር በወታደራዊ ፍጥጫ ውስጥ ያለው የወያኔ በድን በወለጋ ውስጥ አንፊሎ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ አንድ የታጠቀ ኃይል በሰነዘረው ድንገተኛ ጥቃት በፌዴራል ፖሊሶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት መድረሱን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አጋለጠ::

ሐምሌ 20 ቀን 2000ዓ.ም በወለጋ ደንቢደሎ ልዩ ስሙ አንፊሎ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ሰፍሮ በነበረው የፌዴራል ፖሊስ ላይ ለጊዜው ማንነቱ ያልታወቀ ታጣቂ ኃይል በወሰደው ድንገተኛ እርምጃ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት ከመሆኑም በላይ ፖሊሶቹ ለጊዜው ከአካባቢው ሸሽተው ያመለጡ መሆኑን የደረሰን ዘገባ ገልፆ በተለይም ቁስለኞች ወደ ነቀምት ሆስፒታል እና ጦር ኃይሎች ሆስፒታል መጓጓዛቸውን አስረድተዋል::

በሰሜን ከሻዕቢያ ጋር፣ በምስራቅ ከኦጋዴን ነፃ አውጪ ጋር እንደብራና ተወጥሮ ያለው የወያኔ ቡድን በወለጋ ውስጥ ደግሞ አስደንጋጭ በሆነ ሁኔታ የወያኔ ፌዴራል ፖሊስ ላይ ጥቃት መድረሱ የወያኔ ባለስልጣናትን ክፉኛ እንዳስደነገጠ ከደረሰን ዘገባ ለማረጋገጥ ተችሏል::

የወያኔ በድን በተለያየ መንገድ የሀገሪቷን ሀብት እያግበሰበሰ ለጥቂት ግለሰቦች ኪስ እያወለው መሆኑን አሁንም እንደቀጠለበት መሆኑ ተጋለጠ::

መሬት ሸንሽኖ ለሱዳን መስጠቱ ያላረካው ወያኔ ሰሞኑን ደግሞ በሀገሪቱ ውስጥ ያሉትን ጥጃዎች ከሁሉም ክልሎች እየሰበሰበ መቸብቸብ መጀመሩን ከተለያዩ አካባቢዎች የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

ከሐምሌ 3 ቀን 2000 ዓ.ምጀምሮ በወያኔ ከፍተኛ ባለሠልጣናትና በሱዳን ባለሀብቶች መካከል በተደረገ ምስጢራዊ ስምምነት በቀን ከ1000 ሺህ በላይ ጥጆች ወደ ሱዳን እየተጋዙ መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ እነዚህ ሆድ አደር እንጂ ማሰቢያ የሌላቸው የወያኔ ቡድን ጥቅርም ግለቦች ሀገሪቷን ቀንድ ከብት አልባ ለማድረግና የራሳቸውን ኪስ ለማደለብ ብቻ በከፍተኛ ገንዘብ ተሻርከው እየሸጡ መሆኑን አስረድቷል::

ከአፍሪካ ቀንድ በከብቶች ብዛት አንደኛ የሆነችውን ሀገራችንን ከሱዳን ባለሀብቶች ጋር በመመሳጠር ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች በርካሽ ዋጋ በመሰብሰብ ወደ ሱዳን እንዲሸጡ ከመለስ ዜናዊ ጀምሮ ትላልቆቹ ባለሥልጣናት ጭምር ሽርክና ያሉበትን ንግድ መጀመራቸውን የገለፀው የደረሰን ዘገባ ሀገሪቱን በየቀኑ ምክንያት እየፈጠሩ ድህነቷንና ውድቀቷን ለማፋጠን ያላሰለሰ ጥረት እያደረጉ መሆናቸው የተጋለጠበት ወቅት ነው ሲል ዘገባው አስረድቷል::

ያለ ማንም ከልካይ የሕዝብና የሀገር ሀብት የሆኑትን የቀንድ ቀብቶች በቀን ከ1ሺህ በላይ ጥጆች ከቦረና ፤ ከወሎ ፤ከደቡብ፣ ከሐረርና ከሌሎችም ክፍለ ሀገሮች በርካሽ ዋጋ እየሰበሰቡ በጉጃም በኩል ወደ ሱዳን እያስወጡ ሲሆን፣ የዚህ ዋነኛ ተዋናይ ከመለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን ጀምሮ

ትላልቆቹ ባለሥልጣናት በስውር ሽርክና እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል ሲል ይኸው የደረሰን ዘገባ ገልጿል::

በየጊዜው ስልቱን እየቀየረ የሕዝብ እና የሀገር ሀብት የሆነውን ንብረት ለባዕድ አሳልፎ እየሰጠ የግለሰቦች ኪስን በማደለብ ላይ ያለው አውሬ የወያኔ ቡድን ሲሆን ለ17 ዓመታት ያህል ያለማቋረጥ ሕዝብን ለድህነት ሀገሪቷን ለምድረ በዳነት የሚዳርግ ተግባር ሲያከናውን የቆየ መሆኑን ማንም የሚገነዘበው ነው ሲሉ አንዳንድ የሀገር ተቆርቋሪ ዜጐች በቁጭት ይገልፃሉ::

ሕዝቡ በችግር ሲቆላና ሲታመስ ቅንጣት ታክል ያልተጨነቁት እነ መለስ ለራሳቸው ኪስ መደለብ ግን የሀገርንና የህዝብን ሀብት እየሸጡ ቀን ከሌሊት መሩዋሩዋጣቸው አሳፋሪና አሳዛኝ ነው ሲሉም በብስጭት ገልጸዋል::

ረሀብተኛ የለም እያለ ሲምልና ሲገዘት የቆየው የወያኔ ቡድን ሰሞኑን የረሀብ አደጋው ክፉኛ እየተስፋፋ በመሆኑ በአስቸኩዋይ ድረሱልኝ ሲል አለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶችን ተማፅኗ:: ለ7 ወራት ያህል በሀገሪቱ ረሀብ መከሰቱን ሳይገልጽ ደብቆ የቆየ ከመሆኑም በላይ ለጋሽ ድርጅቶች እርዳታ እንዳይሰጡ ምንም ረሀብ በሀገሪቱ አልተከሰተም እያለ ለማታለል ቢሞክርም ዛሬ እውነታው ይፋ ወጥቶ የአለም ህዝብ መሳቂያና ማፈሪያ መሆኑን ለመረዳት ተችሎዋል ሲል የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

በሀገሪቱ ረሀብ መከሰቱን ተገንዝበው ለችግሩ እንድረስ ያሉትን አለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች ምንም ችግር እንዳልተከሰተ በማስመሰል በሩን የቆለፈው አረመኔው የወያኔ ቡድን የረሀብተኛው ቁጥር በእጅጉ በማሻቀቡ የተነሳ ሰሞኑን ለአለም አቀፍ ጋዜጠኞችና ተቀማጭነታቸው አዲስ አበባ ለሆኑ ዲፕሎማቶች የድረሱልን ጥሪ አሰምቶዋል::

በርሀቡ ምክንያት የሰው ልጅ እንደቅጠል በየጎዳና ላይ እየረገፈ ባለበት ወቅት ፈጥነን እንድረስላቸው ፣ አሁን ባጭሩ ካልተቀጨ ረሀቡ የከፋ አደጋ ያደርሳል እያሉ አለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች ቢወተውቱም ቅንጣት ታክል ያልተሰማው ወያኔ ሁሉም ነገር ግራ ሲያጋባውና ማጣፊያው ሲያጥረው ረሀብ መከሰቱንና ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን አምኖ የድረሱልኝ ጥሪ ማቅረቡ ዲፕሎማቶችንና አለም አቀፍ ጋዜጠኞችን አስገርሞዋል::

የወያኔው የግብርናና የገጠር ልማት ሚኒስተር ምክትል ሚኒስትር የኦህዴዱ ካድሬ አበራ ደሬሳና በነመለስ ሳንባ የሚተነፍሰው ስምኦን መቻሌ በጋራ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ እንደ ገለጹት በአሁኑ ሰዓት ቁጥሩ እጅግ የበዛ ህዝብ በረሀቡ የተጠቃ መሆኑንና ሌላም በተመሳሳይ ቁጥሩ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ህዝብ ሊጠቃ እንደሚችል ገልፀው አስቸኩዋይ እርዳታ ይሰጠን ሲሉ አይናቸውን በጨው ታጥበው ጥሪ አድርገዋል::

እርዳታ እንስጥ ሲሉ የነበሩትን አለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች ከጠላት ጋር ወግናችሁዋል እያለ ከሀገር ውስጥ እያባረረ ፤ረሀቡ አደገኛ ነው ያሉትን ደግሞ የኛ እድገት ያላስደሰታችሁ ናችሁ በማለት ሲሳደብና ሲያወግዝ የቆየው የወያኔ ቡድን ዛሬ ከአቅሙ በላይ በሆነ ፍጥነት ሊደበቅ በማይችልበት ደረጃ ላይ መድረሱን ሲረዳ ይፋ መግለጫ ለመስጠት መገደዱን የገለፁት ዲፕሎማቶች ተወደደም ተጠላ እስከ ዛሬ ለተፈጠረው ሰብአዊ ቀውስ ሁሉ ተጠያቂው መለስ ዜናዊና ግብረ አበር ካድሬዎቹ ናቸው ሲሉ አፅንኦት ሰጥተው ገልፀዋል፡፡

በህዝብ ሀብትና ንብረት እንደልባቸው እየተንቀባረሩ ያሉት የወያኔ ባለስልጣናት ከደርግና ከኃይለስላሴ ዘመን በከፋ መልኩ ረሀብ በሀገሪቱ ተንሰራፍቶ ባለበት ወቅት ሚሊኒየም በዓል በሚል ገንዘብ እያባከኑ ዜጎች በየጎዳና ላይ እንደ ቅጠል ሲረግፉ እንደነበር ያስታወሱት አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር ዛሬም ይፋ ያወጡት ተጠያቂ ላለመሆንና ሁሉም ነገር ከቁጥጥራቸው ውጭ ስለሆነባቸው ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በሀገርና በህዝብ ላይ ለ17 ዓመታት ሲያሾፍና ሲቀልድ የነበረው ወያኔ ሕዝብ ያወቀውን ፀሐይ የሞቀውን እውነት ሽምጥጥ አድርጎ ዋሽቶ ረሀብ አልተከሰተም እያለ ለብዙ ዜጎች ህይወት መቀጠፍ ተጠያቂ ሲሆን አሁንም ከወሬ ያለፈ አንዳችም እንቅስቃሴ እያደረገ አለመሆኑንና በአሁን ሰዓት የረሀብተኛው ቁጥር ከ13 ሚሊዮን በላይ መድረሱን የግብርና ባለሙያዎች በሀዘን እየገለፁ ናቸው፡፡